EthioLion

# ህይዎትና ዕረፍቷ

አብርሃም በየነ

በመኖርና ባለመኖር የሚካሄደው ትንቅንቅ

ተፈጥሮ ህይዎትን አድርጓት የሞት ስንቅ

የሰው ልጅ የመኖር ህላዌ ተስፋ

ህይዎት በሞት ጥላ ስር አርፋ

መኖሯ በሞት መስተንግዶ ሲጠፋ

ክስተቱ ዘንታለም ባይተዋር እንግዳ

ሞትን ያደርገዋል የሰው ልጆች ዕዳ።

ሞትን ያወረሰው ሰው የመሆኑ ተፈጥሮ

ከመኖሩ ህላዌ ጋር አለመኖሩም ተጣምሮ

ሩሁ እስክትወጣ የሚኖረውን ዕድሜ

እርዝመቱን ሲጠብቅ በማጠሩ ፍጻሜ

የሰው ልጅ ሲኖርና ሲሞት

ሁሌም ይሸበራል በሞት እንግድነት።

ሞት ፀጋም ይሆናል፤ የህይዎትም ዕዳ

መኖር የሚከፍለው

አንድም አመሻሽቶ አንድም በማለዳ።

...............  . . / /..................

ይህች ግጥም መታሰቢያነቷ ለወንድሜና ወድ ጓዴ ለአፈወርቅ ደጀኔ ትሁን።

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!